# <u>አያያዛችን አይተው...</u>

*ዳደ ደስታ*

dadeyom@gmail.com

‹እኛና ግብጽ› በሚለው ማስታወሻዬ የግብጽና ናይል ጉዳይ ለኛ ምን ያህል ብልሃትና ትኩረት የሚጠይቅ ቀዳሚ-ውስብስብ-አንገብጋቢ ጉዳይ እንደሆነ ለመጠቆም ነበር የሞከርኩት። ይህኛውም ከዚያው እሚለጥቅ ነው፤ ግን በኢትዮጵያ የፓሊሲ አቋዋሞች ላይ የከረረ ትችት ስዘነዝር ብታነቡኝ፣ ምክንያቴ የጉዳዩ አሳሳቢነትና የኛ ስንፍና ያስከተለብን ዕዳ ከማየት እንጂ ሌላ መነሻ ኖረኝ አይደለም። ከቀናኝ፣ የሚመለከታቸው የፖሊሲ ኃላፊዎቻችን እንዲያጤኑት፣ ካልሆነም ቁጭቴን አጋራለሁ በሚል ነው።

### 1) እየሰጡ መሸሽ

*ምሳሌ ላቅርብ። እንበልና፤ አንድ ቤት አለ። እዛው ቤት ውስጥ ላሉት የቤተሰብ አባላት ዕለታዊ የውሃ ፍጆታቸው አንድ በርሚል ውሃ ነው። በርሚል ውሃዋ ብትጎድል፣ እዛ ቤት ውስጥ ህይወት ትስተጉዋጎላለች። ነገር ግን አንድ የውጭ ሰው ጥዋት ጥዋት አንድ ሙሉ በርሚል ውሃ እያንከባለለ አምጥቶ እዛው ቤት አድርሶት ይሄዳል። በምላሹ ዋጋ ጠይቆ አያውቅም፤ አንዲትም ቃል ትንፍሽ ብሎ አያውቅም፤ አንድም ቀን ቀርቶና አቋዋርጦ አያውቅም። ለዘመናት እንዲዚሁ ቀጠሉ። በአቀባዩና በተጠቃሚው መካከል ያለው ግንኙነት ልክ አይመስልም። በሰብአዊነትና በቅድስና እነዲመዘገብለት ካልፈለገ በቀር እዛ ቤተሰብ ላይ የፈለገውን ያህል ተጽእኖ ማሳረፍ ይችል ነበር፣ የያዘው ነገር የጉሮሮ ጉዳይ ነውና። ነገር ግን ደግሞ ግልብጥብጡ በወጣ የተገላቢጦሽ ሁለታዊ ግንኙነት አዛዡ ናዛዡ ውሃ ሰጪው ሳይሆን ተቀባዩ ሆነ!*

በናይል ላይ የኢትዮጵያ ፖሊሲ ይዘትና አቀራረብ እንደ ውሃው ህይወት ያለውና ያለማቋረጥ የሚፈስና ወራጅ መሆኑ ቀርቶ መሃንና ደረቅ ነው። ህይወት ያለው የፖሊሲ አቀራረብ ለመባል ትክክለኛና በመርህ የተመሰረተ ፖሊሲ ሆኖ መቀረጹ በቂ አያደርገውም። እሚፈስና እሚንቀሳቀስ ፖሊሲ መሆን አለበት። በቂ እሚሆነው በየጊዜው ራሱን ለማስተዋወቅና ጥቃቅን ማሻሻያዎችንም በየወቅቱ ለማካተት እሚያስችል dynamic and self corrective እንዲሆን የሚያበቁት አሰራሮች የተበጁለት እንደሆነ ነው። አሁን ኢትዮጵያ በናይል ያላት የፖሊሲ ይዘትና አቀራረብ እንኳዋን ወራጅ ሊሆን እርጥብም አይደለም። አንድ ቦታ ላይ የተቸከለና ሙት ነው። ‹‹አንድ ቀን የዓባይን ዉኃ ገድበን እንጠቀማለን፣ አንድ ቀን ግብጻውያን ክፋት-አልባ ቀና ምኞታችንን ይረዱልናል፣ አንድ ቀን በቂ የራስ ጥንካሬ ገንብተን በገዛ ውሃችን ለመጠቀም ከሌሎች የምንጠብቀው ፍቃድ አይኖርም.. ወዘተ›› በሚሉ ስሜቶች የተቃኘ ፖሊሲ ነው ያለን። የቅርብ ጊዜው የህዳሴ ግድብ እናቆየውና፣ በዛሬዋና በምትጠበቀዋ ቀን መካከል ግን የመዳረሻ ክንዋኔዎች ያለማቋረጥ ሲደረጉ አይታዩም። ያለማቋረጥ እሚፈሰው የአባይ ዉኃ ነው።

እንደወንዙ ሁሉ የኢትዮጵያ መልዕክትና ጉትትም አሳማኝ ፍትህና ወዳጅነት ተሸክሞ በየዕለቱ ቁልቁል አብሮ መፍሰስ ነበረበት። ያ ቢሆን ኖሮ የናይል ውሃ ህይወታችን ነው የሚለው የግብጽ ህዝብ በየዕለቱ የህይወት ውሃ የሚሰፍሩለትን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ያለ እጃቸው በጥርጣሬና በጠላትነት አያያቸውም ነበር። ያ ቢሆን ኖሮ "ውሃ ከደም ይወፍራል" እሚሉት ግብጻውያን "የውሃ ወንድም ከነዳጅ ወዳጅ በላይ ነው" ይሉ ነበር። በወንዙ ወስጥ ያሉት ዓሳዎች፣ ዓዞዎች፣ ዕጽዋት ሁሉ የኢትዮጵያን ስም እያነሱ የዘወትር ምስጋናና ውዳሴ ያሰሙ ነበር። ያ ሁሉ ቀርቶ የኢትዮጵያ ስም እሚነሳው የህይወት ሳይሆን የስጋት ምንጭ ተደርጋ ነው። በተቃራኒው ደግሞ ግብጾች በናይል ላይ ያላቸው ፖሊሲ ራሱን እያደሰና ከሁኔታዎች ጋር ራሱን እያስተካከለ የሚጓዝ እንጂ የቆመ አይደለም። የኛ ዉሃ ያለፋታ ቁልቁል ወደነሱ እየፈሰሰ ህይወት ሲመግብ፣ የነሱ ክፋት ደግሞ ያለፋታ ሊያውከን ሽቅብ ወደኛ

ይተፋል። ውጤቱም ጤፍ ላበደረ ጠጠር ሆኖ እስከ አሁን ዘልቀናል። ግን መፍረድ ያለብን በራሳችን ላይ ነው።

የኢትዮጵያ፣ የግብጽና ሱዳን ህዝቦች ቁጥር አሁን ከሁለት መቶ ሰላሳ ሚልዮን በላይ ደርሷል። አጠቃላይ የናይል ተፋሰስ አገሮችን ካሰብን ደግሞ ግማሽ ቢልዮን ሊመታ ትንሽ ፊሪ ነው። ይህ ጥንተ ስልጣኔና ታሪክ ብቻ ሳይሆን ባለንበት ዘመን ሰፊ ማህበረሰብ፣ ሃብትና ገበያ የተከማቸበት አካባቢ ነው። የራሳችን አውድማ ነው። እንደዋዛ እሚታይ እና ለዘፈቀደ እሚተው አካባቢ አይደለም።

ከያንዳንዷ ጠብታ ውሃ ጋር እሚላክ በጎ ተጽእኖና የትብብር መንፈስ እሚገነቡ መልእክቶች ማፍሰስ ይኖርብናል። የወራጅ ውሃው ታዳሽ ጉልበትና የርቱዕ አቋሞቻችን ስለት ለጋራ ጥቅሞቻችን መጠቀም አለብን። በዛውም እኛ ራሳችንን ብቻ ሳይሆን አካባቢውንም ከዜሮ ድምር ፍጥጫ ወጥቶ የብዙዎች ተጠቃሚነት የሚረጋገጥበት አከባቢ ወደ መሆን ይሻገራል። ሚልዮኖች ከጎስቋላ ኑሮ ይላቀቃሉ። ይህ ኢትዮጵያ ካልሰራችው ማን ይሰራዋል?!

## 2) ድፍርስ ዐይነ-ውሃ

ለአፈራችን ምስጋና ይግባውና፣ የአባይ ዉሃ ድፍርስ ነው። እንደዚሁም፣ ኢትዮጵያ በውሃው ያላት አመለካከት ያልጠራ ድፍርስ ነው።

ዓባይ ለኢትዮጵያ ከጠቀማት የጎዳት ይበዛል። አንድ ቀን ይጠቅማት ይሆናል ከሚል እሳቤ ካልሆነ በቀር እስከአሁን እንደ ሃብትም እንደ ስትራተጂክ መቋሚያ ወይም leverage depth ወዳጅነት ከማብዛት አንጻርም ለኢትዮጵያ ያበረከተላት ነገር ኢምንት ነው። በተቃራኒው ግን ብዙ ጉዳት አድርሷል። ይህም የወንዙ ወይም የዉሃው ችግር ሳይሆን ኢትዮጵያ ለወንዙ ወይም ለውሃው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ላይ ብቻ በማትኮር ለጂኦፖለቲካዊ ከዋኝነቱ እምትሰጠው ፍቺ (definition) የጠራ መነሻ ስለሌለው ነው። በአንጻሩ ግብጾች የጠራ መነሻ አላቸው። የናይል ውሃን እሚያዩት እንደ እስትንፋሳቸው ነው፣ የሞትና የህይወት ጉዳይ አድረገው። ለነሱ የደህንነታቸው ብቻ ሳይሆን የህልውናቸው ጉዳይ እንደሆነ ቆጥረው የመጨረሻ ከፍታ ያለው ስፍራ ይሰጡታል። በናይል ዉሃ ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ማሳረፍ እሚችልን ኃይል ሁሉ የግብጽ የደህንነትና ህልውና መነጽር ሰክተው ነው እሚመዝኑት። ያ ማለት ደግሞ እነሱ እማይቆጣጠሩት የናይል ተፋሰስ ሁነኛ ተጽእኖ ፈጣሪ ኃይል እንዳይፈጠር፣ ከተፈጠረም ጎልቶ እንዳይወጣ፣ ያላቸውን ሁሉ አሚጠው በሙሉ አቅማቸው ይረባረባሉ።

በናይል ዉሃና ተፋሰስ ዙርያ ያለው ግጭት ፈጽሞ ምክንያት የለሽ አይደለም። እንደውም በዓለም ላይ ከሚከሰቱት ድንበር ዘለል ግጭቶች እንደ ናይል አገሮች ግጭት ዓይነት ግልጽና ምክንያታዊ ፍጥጫ የለም። ውሃው ከኢትዮጵያ ይነሳል። የውሃው የመጨረሻ መዳረሻ ግብጽ ናት። ግብጽ ይህን ውሃ እምታየው Extreme Securitization በምንለው ጽንሰ ሃሳብ ደረጃ የህልውና ጉዳይና ስጋት በሚል ነው። ለኢትዮጵያ ውሃው ቅምጥ ጸጋ እንጂ የደህንነትም የህልውናም ጉዳይ አይደለም። ስለዚህ የኢትዮጵያ ዕይታ ከSecuritization ዉጭ ማለት ነው ። እኛና እነሱ እምናይበት ደረጃና መነጽር ይለያያል። ያ ማለት ለጉዳዩ የምንመድበውም ቀልብ (commitment) ለየቅል ነው። የኛ ትልቁ ህጸጽ እዚህ ላይ ነው። ግብጽ የህልውና ጉዳይ አድርጋ እስከያዘችው ድረስ ኢትዮጵያ በውሃው ላይ "ለምታደርገው እንቅስቃሴ" የግብጽ ምላሽ የራሷን "ህልውና" የማስጠበቅ ያህል ፋይዳ ይኖናጸፋል። "ለምታደርገው እንቅስቃሴ" አልን እንጂ "አንድ ቀን ልታደርግ ትችላለች ወይም ታስባለች" እሚለውም ምናልባታዊ ስጋት በቂ ነው። ይህ ፈጽመው ከማይሸሹትና ከማያመልጡት እርግማን ይቆጠራል። የፍትህ፣ የጥቅምና የመብት ጉዳይ ትተን ለግብጽ በመሃላም በተግባርም፣ በዓባይ ጉዳይ ላይ ‹እኛችን አናናሳም› የሚል ማረጋገጫ ብንሰጥም እንኳ እማንገላገለው እርግማን ነው። እንዲያም ሲባል በዉጤቱ፣

ግብጽ በምትወስደው እርምጃ ምክንያትና መንስኤ ራስን ወይም የራስን ጥቅም ለመከላከል ከሚመነጭ አስገዳጅ ሁኔታ ለኢትዮጵያም የህልውና ጉዳይ ማለትም effected securitization ሆኖ ይወጣል።

ኢትዮጵያ ለብዙ ግጭቶችና ብጥብጦች የተዳረገችውና እየገባች ያለችው በዓባይ ምክንያት ነው። ኢትዮጵያ በአረቦች ምድር በከፍተኛ ጥርጣሬና ጥላቻ እንድትታይ የሆነችው በዓባይና በግብጽ ምክንያት ነው። ኢትዮጵያ ዘላለሟን በድንቁርናና በድህነት ተገምዳ፣ መሰረታዊና ህይወት ቀያሪ የሆኑ ልማቶች አከናውና ህዝቦቿን ከእርዛት የሚገላግል አቅጣጫ ቀይሳ ወደ ልማትና ዕድገት እንዳትገሰግስ ቁልፍ አደናቃፊ ሚና የምትጫወተው ግብጽ ናት። ግብጽ ይህንን እምታደርገው ወይ አስቀድማ ነገሮችን ለመቆጣጠር በምታበጃቸው ቅድመ-ማርከሻዎ□ አለዛም የኢትዮጵያን ዱካ እግር በእግር እየተከታተለች ጅማሮዎችን በማክሸፍ ነው። ግብጽ ይህን ጨዋታ የተሳካላት፣ ኢትዮጵያ ደግሞ በተቃራኒው ሆና የተገኘችው ለምንድነው? ምክንያቱ ብዙም የተሰወረ አይደለም። ግብጽ የሙሉ ትኩረትና ግዜ ሥራ፣ ኢትዮጵያ ደግሞ አንድ ቀን ሁኔታዎች ሲመቻቹላትና ዕድል ስታገኝ ብቻ እምትመለስበት የይደር አጀንዳ አድርጋ ስለምታየው ነው። ያ ዕድል ግን ሁሌ ለሚሰራ እንጂ ሁሌ ለሚጠብቅ አይመጣም።

የጠራ አመለካከት ሲባል መነሻ ሃሳቦቹ ምን ይመስላሉ ብንል የሚከተሉትን ነጥቦች እንይ፤ ዓባይ ዝም ብሎ እሚፈስ ወንዝ ብቻ አይደለም። ዉሃ አፈር ይዞ ሄዶ ነገር ይዞ እሚመጣ ጸጋና እርግማን ነው። ‹ይሂድ ማደርያው ይፈልግ አንድ ቀን እንመለስበታለን› ሲባል መመለሻው እንዳያጥር እሚያደርጉ ውስብስብ ሁኔታዎች በየጊዜው እምታደራው ግብጽ ደግሞ ያለ እንቅልፍ በትጋት በሚፈሰው ዉሃ ልክ ነገር ታፋስብናለች። ዉሃ ለመገደብ ከምንተጋው በላይ በውሃው ምክንያት ያለማቋረጥ እሚፈስብንን የነገር ወንዝ ለመገደብ የጠራ መነሻና የማያቋርጥ ሥራ እንደሚጠይቅ ማሰብ ማለት ነው።

ናይል በተፈጥራዊ መስመሩ ሳይዛነፍ ይፈሳል። የናይል ጂኦፖለቲካዊ ጉዳዮች ግን ከመስመር ወጥተው ከኢትዮጵያ ቁጥጥር ውጭ ይፈሳሉ። ዕዳውም ለኢትዮጵያ ነው። ይህ በእስከ አሁኑ ታሪካችን ያረጋገጥነው ሃቅ ነው። ይህን የተዛነፈ ሁኔታ ለማቆም እሚያስፈልገው የናይል ጉዳይ አንገብጋቢና ይደር እማይባል አጀንዳ መሆኑን አምኖ የቅድሚያዎች ሁሉ ቅድሚያ ትኩረት ከመስጠት ይጀምራል።

### 3) ተሰላፊውን ወይስ አሰላፊውን

ታዳሚዎቹን፣ ሜዳውን፣ ተጫዋቾቹንና ቁልፍ ተጫዎቾቹን እንደየደረጃቸው መለየት ያለመቻል፣ ወይም የቅደም ተከተል ምዘናዎቹን ማምታታት፣ ወይም ከዚሁ ሁናቴ በሚመነጭ ድክመት ምክንያት የአትኩሮት ምደባውን ማዛባት ዋጋ ያስከፍላል፤ ያውም አገርን።

ታዳሚዎቹ ሁሉም (ማለትም፣ የቅርቦቹም የሩቆቹም) ዓለማቀፋዊ ጂኦፖለቲካዊ ኃይሎች ናቸው። ኃያላን አገሮችና ዓለም ባንክን የመሳሰሉ ዓለም ዓቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪ ተቋማት እዚህ ዉስጥ ይካተታሉ። ተመልካቾቹም ጨዋታው ላይ ተጽዕኖ የማሳረፍ ሚና አላቸው። ሚናቸው ግን ከቁልፍ ወይም አውራ ተጨዋቹ ፍላጎት ጋር የተጣጠመ ነው። ሜዳው የናይል ተፋሰስ ቀጣና ሲሆን ተጨዋቾቹ ደግሞ አስራ አንዱ የናይል ተፋሰስ አገሮች ናቸው። አስራ አንዱ ተጨዋቾች አንድ ሜዳ ላይም ቢሆኑ ግባቸውም አሰላለፋቸም ለየቅልና ለግል ነው። እንዲያም ሆኖ ጨዋታውን የመቆጣጠር ብቃታቸው ሲታይ ከልምድም፣ ከፍላጎትም ከተጨባጭ ዓቅምም አንጻር የተለያየና የተራራቀ ነው። ሜዳው ገለልተኛ ነው፣ የተጫወተውም ያልተጫወተውም እኩል ያስተናግዳል። የቲፎዞዎቹ የማድመቂያ ድጋፍና ውግንና ግን የጎላ ብቃት ላለው የአውራዎቹ አውራ ተጨዋች ሆኖ በታማኝነት ዘልቋል። በሌላ አገላለጽ፣ ሜዳው ዉስጥ ለመግባት የተፋሰሱ ተወላጅ መሆን ብቻ ሲጠይቅ፣ ቲፎዞዎችን ማፍራት እሚቻለው ግን የራስን ብቃት በማሳደግ ብቻ ነው።

ከኢትዮጵያ አንጻር የናይል ተፋሰስ ተጫዋቾች በሁለት ምድብ ተከፍለው መታየት አለባቸው። ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብጽ አንደኛው ምድብ ዉስጥ፣ የተቀሩት ማለትም ደቡብ ሱዳን፣ ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ዲ. አር ኮንጎ፣ ብሩንዲ፣ ርዋንዳና ኤርትራ ደግሞ ሁለተኛው ምድብ ዉስጥ። ከናይል ወንዝ እንዲያም ሲል ከኢትዮጵያ ጥቅሞችና ጉዳቶች አንጻር አውራዎቹ ተጨዋቾች ያሉት የመጀመርያው ምድብ ላይ ነው። የናይል ተፋሰስ ሜዳ ጨዋታ እሚወሰነው በኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብጽ ነው። ይህ ሁነኛ የናይል የስበት ማእከል በልኩ መታወቅ፣ በዚያው ልክም የኢትዮጵያ ትኩረት ማዕከላዊ ስበት መሆን አለበት።

ሌሎች ኃይሎች በሁለተኛና በሶስተኛ ደረጃ እሚታዩ ናቸው። ሶስተኞቹን እንይ። እነዚህ በናይል ዉሃ ሃብት ላይ ቀጥተኛ የባለድርሻነት ሚና የሌላቸው ግን በዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪነታቸው ወሳኝ የገንዘብና የፖለቲካ ድጋፍ ማቅረብ እሚችሉ ኃይሎች ናቸው። ድጋፋቸውም ለሚፈልጉት ኃይል በመስጠት ብቻ ሳይሆን እነሱ የሚፈልጉት ኃይል ያልደገፈውንም ወገን ድጋፍ ከመንሳት እስከ ዕንቅፋት መሆን የዘለለ ወሳኝ ሚና አላቸው። በነዚህ ኃይሎች ተፈላጊ መሆን በአቤቱታና በማመልከቻ እሚገኝ አይደለም። ለተፈላጊነት ብቁ ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል። ይህ ለግብጽ የተሳካላት ጨዋታ ነው። ኢትዮጵያ በዚህ ግንባር በከባድ ትጋት ተንቀሳቅሳ የተወሰነ ዉጤት ብታገኝ ነው እንጂ ግብጽን ተወዳድራ ለማሸነፍ አሁን ባሉት ሁኔታዎች ያለው ዕድል ጠበብ ያለ ነው። ዕድሉን ለማስፋት ሁኔታዎች መቀየር ይኖርባቸዋል። ሁኔታዎች እሚቀየሩት ደግሞ የማዕከላዊ ስበት ሚዛን በማዛባት ነው።

ሁለተኞው ረድፍ ላይ ያሉት የናይል ተፋሰስ ተጫዋቾች ቢሆኑም ግንባር ቀደም ተሰላፊዎች አይደሉም። የናይል ጉዳይም እንቀልፍ እሚነሳቸው የቅድሚያ ቅድሚያ ጭንቃቸው ሊሆን አልበቃም። በናይል ጉዳይ ባለድርሻ ቢሆኑም የግርጌዎቹ ስጋት ባለመሆናቸው ቅሉ ዋናውን ክብደትና ኃላፊነት የተሸከሙ ባለጉዳዮች ግን አይደሉም። የጨዋታውን ቀመርና ስበት ለመቀየር ጠቃሚ አጋሮች ሊሆኑ ቢችሉም ቁርጠኝነትና ወሳኝነት ያንሳቸዋል። የኢትዮጵያ የፖሊሲ ትኩረት ግን እነዚህኞቹ ላይ ተቀርቅሯል። ይህም የአቅጣጫ ስህተት ሆኖ ይታያል። እርግጥ ነው፤ ኢትዮጵያ እነዚህን ወገኖች በማነቃነቅ የጨዋታ ሚዛኑን ለመቀየር በትጋት እየተንቀሳቀሰች ነው። ነገር ግን በብዙ ድካም የገነባችውን የናይል ትብብር ግብጽ በአንድ ጀምበር ብትንትኑን ስታወጣው ይታያል። ይህ የሚሰጠው ምልክት የኢትዮጵያ ርብርብ ተሰላፊው ላይ መሆኑ ቀርቶ አሰላፊው ላይ መሆን እንዳለበት ነው

## 4) ግብፃዊ ወዳጆች ፍለጋ

የግብጽ ኤሊቶችን፣ የግብጽ መንግስትንና የግብጽ ህዝብን በአንድ በኩል እንደ አንድ ቅይጥ ገበታ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ በያይነቱ መዓድ በመፈረጅ የዋናውን ኃይል አመለካከት ለማስቀየር እሚሰራ ዲፕሎማሲ ያለመገንባት ችግር፣ አጀንዳ አቅራቢዎች መሆናችን ቀርቶ ሸባና አጀንዳ ጠባቂዎች አድርጎናል።

አሁን እያጠበብን እዚህ ደርሰናል። ከጂኦፖለቲካዊ ችግሮቻችን ሁሉ ጎልቶ እሚታየው የናይል ተፋሰስ ኃይሎችና አሰላለፍ እንደሆነ ጠቁመናል። በመሆኑም የዲፕሎማሲውም ዋነኛ ትኩረት እዛው ጉዳይ ላይ መሆን እንደሚገባው አመላክተናል። ቀጥሎ ከኢትዮጵያ ህልውናና ጥቅም አኳያ፣ ማእከላዊ ስበቱ ግብጽ ላይ እንደተሰበሰበ አውስተናል። አሁን ግብጽ ዉስጥ ራሱ ዋነኛው የትኩረት ዒላማ የት ላይ ማነጣጠር እንደሚገባ በአስረጅ አስረግጠን ለማሳየት እንሞክራለን።

ኢትዮጵያ ቅድም በጠቀስናቸው የትኩረት አቅጣጫ መዛባት ምክንያት ከግብጽ መንግስት ጋር ያላት ግንኙነትና መስተጋብር በአሉታም፣ በአዎንታም የጉዳዩን ግዝፈትና ውስብስብነት የሚጠይቀውን ያህል የተጧጧፈ አይደለም። ከኢትዮጵያ በኩል ያለው ግብጽ ላይ ተጽእኖ የማሳደር ዲፕሎማሲ ወይም

ግንኙነት ሁኔታውን የሚመጥን ሳይሆን የላላ ነው። ሁኔታውን ለመለወጥ እሚያበቃ መሆኑ ቀርቶ ለግብጽ እንቅስቃሴም አጸፋ ከመስጠት አኳያም ቢሆን ዝቅተኛ ነው።

የለየለት ጦርነትም ባይሆን ግብጾች ብዙ ነገር የማድረግ ዓቅም አላቸው። የማድረግ ችሎታቸውም እስከ አሁን ስንቀምሰው ኖረናል። ከዚያም በላይ ማድረግና መጉዳት ይችላሉ። የሌሎች ኃይሎች እጆች ተጠቅመው የመጉዳት ጥበባቸውም ለረዥም ጊዜ ጥርስ የነቀሉበት ሞያ ነው። ሚካኤል ምናሴ በአንድ መጣጥፉ ይህንን ዘዴያቸው ‹ተውሪት› ሲል ይገልጸዋል። ኢትዮጵያ ግዙፍ ህልምና ኢኮኖሚ ይዛ የባህር በር የሌላት አገር ናት። መውጪያዋና መግቢያዋም ቀይ ባህር ነው። ግብጽ ሁሉንም የቀይ ባህር አገራት ለፍላጎቷ የማንቀሳቀስ አቅሟ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ይህ አንድ የስጋት ምንጭ ነው። ሌላው ግብጽ የስዊዝ ካናልን በር የምትቆጣጠር ኃይል ናት። የሊሎች አገሮችም፣ እሚበዛው የኢትዮጵያ ወጪና ገቢ ንግዶች እሚተላለፈው በዚሁ ነው። በአንድ ቃል፡ ግብጽ ራሷን፣ በአካባቢያችን ያሉት ኃይሎችን፣ ኢትዮጵያ ዉስጥ እሚንቀሳቀሱት ተስፈኛ ፖለቲከኞችን፣ ራቅ ብለው ያሉትን ኃያላን አገሮችን ኢትዮጵያን ለመጉዳት የማሰማራት ቀላል የማይባል ችሎታ ያላት አገር ናት። ለኢትዮጵያ ከግብጽ ሰፊ ህዝብና ተራማጅ ኃይሎች ጋር መግባባትና ዝምድና እሚያጠናክሩ ክሮችን ማብዛት ይደር እማይባል ሥራ መሆን የነበረበት ዛሬ ሳይሆን ትላንት ነበር፤ ነገ ሳይሆን ዛሬ ነበር። ይህ ሁሉ መቀየር የነበረበት፣ ያለበት ምክነት ነው። ለውጡ በህዳሴው ግድብ መጀመሩን ልብ ብለናል። ...ይቀጥላል...